Seattle Department of Education & Early Learning

brightspark early learning services

# የሲያትል ከተማ የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ ክፍያዎች ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች ለልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች

**1.) የዚህ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ዓላማው ምንድነው?**

የዚህ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ዓላማ በሲያትል ከተማ ውስጥ በሚገኙ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች ውስጥ ሲሠሩ ለነበሩ የቅድመ ትምህርት አስተማሪዎች እና የልጅ እንክብካቤ ሠራተኞች የገንዘብ ድጋፍ እና እውቅና መስጠት ነው።

የሲያትል ከተማ የDCYF ፈቃድ ለተሰጣቸው የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች ብቁ ሰራተኞች (FCCs) እና በማእከል ላይ ለተመሰረቱ ፕሮግራሞች ከከተማው የደመወዝ ወጭ ታክስ እስከ $5.3 ሚልዮን ዶላር መድቧል። እነዚህ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ክፍያዎች በሲያትል ከተማ ወሰን ውስጥ ላሉ ፕሮግራሞች ብቻ ይሰጣሉ።

የሲያትል የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት መምሪያ (DEEL) እና BrightSpark የቅድመ ትምህርት አገልግሎቶች እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች ለመሸለም እና ለማከፋፈል በመተባበር ላይ ናቸው።

**2.) ለሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ ክፍያዎች ለማመልከት ብቁ የሆነው ማነው?**

ለእነዚህ የድጋፍ ገንዘቦች ማመልከቻ በአሠሪው/በቀጣሪው መቅረብ አለበት። በቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ጉዳይ ከሆነ፣ ይህ ፈቃድ ያለው ነው። እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች የሚቀበሉ የንግድ ተቋሞች ገንዘቡን ለሰራተኞቻቸው የማስተላለፍ ሃላፊነት አለባቸው።

***ብቃት የሚያሟሉ ሰራተኞች መግለጫ:***
ከዚህ በታች ያሉት ሌሎች መስፈርቶች ሁሉም ከተሟሉ፣ የሙሉ ጊዜ ሥራ ወይም የትርፍ ሰዓት ቅጥር ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በDCYF ፈቃድ የተሰጠው የልጅ እንክብካቤ ማእከል ወይም የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ውስጥ በቦታው ላይ የሚሰሩ ሁሉም የልጅ እንክብካቤ ሠራተኞች ለዚህ የማቆያ ክፍያ ብቁ ይሆናሉ።

ተጨማሪ መስፈርት...

- ሰራተኛው ሰው ቢያንስ ከመጋቢት 1 ቀን 2023 ጀምሮ በፕሮግራሙ ውስጥ ተቀጣሪ ሆኖ የቆየ እና ማመልከቻው በገባበት በዚያን ጊዜ ብቃት ባሟላው የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ውስጥ ተቀጥሮ መስራቱን የቀጠለ።
- ሰውዬው/ ሴትዮዋ ፕሮግራሙ የሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሠራተኞች የማቆያ ክፍያ በሚቀበልበት ጊዜ፣ አሁንም ጥያቄውን የሚያስገባው፣ ብቁ የሆነ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ሠራተኛ፣ እና ፕሮግራሙ ይህንን ክፍያ ብቁ ለሆኑ ሰራተኞቹ በሚሰጥበት ወቅት ተቀጣሪ የሆነ።
- ሰራተኛው ሰው በቦታው ላይ ተገኝቶ የሚሰራ፣ ለልጆች ቀጥተኛ እንክብካቤ የሚሰጥ እና ለአብዛኛው የስራ ፈረቃ ከልጆች ጋር አብሮ የሚሰራ ወይም የሚያገለግል መሆን አለበት። ከክፍል ውስጥ መምህራን፣ ረዳት አስተማሪዎች እና ብዝሃን ክፍሎች ከሚሸፍኑ አስተማሪ ሰራተኞች በተጨማሪ፣ ሥራቸው በቦታው ላይ ተገኝቶ የሚሰራ እስከሆነ፣ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ተቀጣሪ እስከሆኑ፣ እና ሌሎች የብቁነት መስፈርቶችን ያሟሉ እስከሆኑ ድረስ እንደ ልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም የምግብ ዝግጅት፣ በልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም የተመዘገቡ ልጆችን የማጓጓዝ ሚናዎች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ወይም ፕሮግራሙን የሚደግፉ የአስተዳደር ሰራተኞች ለብቁነት ይታሰባሉ። እነዚህ ሚናዎች ሁሉም ፕሮግራሙን "ያገለግላሉ" እንዲሁም አሰራሩን ያስችላሉ።
- ሰራተኛው በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ በሚገኝ የልጅ እንክብካቤ መስጫ ተቋም ውስጥ እስከሰራ ድረስ፣ እርሱ እራሱ የሲያትል ነዋሪ መሆን አያስፈልገውም።
- ያልተቀናጀ ኪንግ ካውንቲን ጨምሮ፣ ከሲያትል ውጭ ያሉ ፕሮግራሞች ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይደሉም። ለትምህርት እድሜ ለደረሱ ብቻ፣ በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ የሚሰሩ ከፍቃድ ነጻ የሆኑ አቅራቢዎች ብቁ አይደሉም። ቤተሰብ፣ ጓደኛ እና ጎረቤት (FFN) ተንከባካቢዎች ብቁ አይደሉም።

**3.) እኔ የDCYF ፍቃድ በተሰጠው ተቋሜ ከልጆች ጋር በቀጥታ የምሰራ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ነኝ። ለዚህ የእውቅና ክፍያ ለራሴ ማመልከት እችላለሁ?**

አዎ። የተቀጠሩ ሰራተኞች ሊኖርዎ አያስፈልግም። ከላይ በጥያቄ #2 ላይ እንደተገለጸው በቀጥታ ከልጆች ጋር የሚሰራ ወይም "የሚያገለግል" የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ (FCC) አቅራቢ ከሆኑ እና የDCYF ፍቃድ የተሰጠው የንግድ ተቋምዎ በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፣ እራስዎን እንደ ብቁ ሰራተኛ መቁጠር ይችላሉ። እባክዎን ልብ ይበሉ፣ ከላይ በ#2 የተገለጹትን “የተቀጠረው በ” መመዘኛዎች ለማሟላት የእርስዎ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም ከመጋቢት 1 ቀን 2023 ጀምሮ ክፍት የDCYF ፈቃድ ሊኖረው የተገባ ነው።

**4.) እንደ አንድ ፈቃድ ያለው የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ወይም ማእከልን መሰረት እንዳደረገ የአገልግሎት አቅራቢ፣ ለዚህ የድጋፍ ስጦታ ብቁ ለመሆን ክፍት መሆን እና ልጆችን ማገልገል አለብኝ?**

በአሁኑ ጊዜ ክፍት መሆን እና ልጆችን የሚቀበሉ መሆን አለበት። በ2023 ውስጥ የእርስዎ ፕሮግራም ቢያንስ አንድ ልጅ የመዘገበ እና ያገለገለ መሆን ይኖርበታል።

**5.) ሰራተኛ የማቆያ ክፍያ (እንደ የድጋፍ ስጦታ ያሉ) መጠኖች ምን ያህል ነው?**

ብቁ ነው ተብሎ የተወሰነው እያንዳንዱ የልጅ እንክብካቤ ሠራተኛ ተመሳሳይ መጠን ይቀበላል። ፕሮግራሞች ለአንዳንድ ብቁ የሆኑ ሰራተኞች ከሌሎች ብቁ የሆኑ ሰራተኞች የበለጠ ክፍያ እንዲከፍሉ <u>አይፈቀድላቸውም</u>። ይህ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞች ከትርፍ ሰዓት ሰራተኞች ወይም በፕሮግራሙ ውስጥ ያለን ሚና መሰረት ያደረገ ልዩነት ምንም እንደማይፈቀድ ያካትታል። ለአንድ ሰው በወከፍ የሚሰጠው/ የሚሸለመው ጠቅላላ መጠን፣ በአመልካቾች ተለይተው በታወቁ ብቁ ሰራተኞች ጠቅላላ ብዛት ላይ ይወሰናል።

**6.) ይህ የገንዘብ ድጋፍ ተወዳዳሪነት ያለው ነው? (የእኔ ማመልከቻ በመጀመሪያ ገብቶ ከሆነ ልዩነት ይኖረዋል?)**

አይ። የማቆያ ክፍያው ስጦታ አሰጣጥ/ አሸላለም በውድድር አይደለም። የብቃት መስፈርቱን የሚያሟሉ እና እስከ የማመልከቻው የማብቂያ ጊዜ ድረስ የሚያቀርቡ አመልካቾች ሁሉም በእኩልነት ይታሰባሉ።

**7.) ብቁ ለመሆን የ Working Connections Child Care የስቴት ድጎማ የሚያገኙ ቤተሰቦችን ማገልገል ወይም በልጅ እንክብካቤ እርዳታ ፕሮግራም ውስጥ (CCAP) መመዝገብ አለብኝ?**

አይ። የስራ ግንኙነቶች (WCCC) ወይም የልጅ እንክብካቤ እርዳታ ፕሮግራም (CCAP) ድጎማዎችን ቢቀበልም ባይቀበልም፣ ማንኛውም በሲያትል ከተማ ገደብ ውስጥ የDCYF ፍቃድ የተሰጠው የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ማመልከት ይችላል።

**8.) ብቁ ለመሆን በ Early Achievers ውስጥ መመዝገብ አለብኝ?**

አይ። ይህ መስፈርት አይደለም፣ ወይም በ Early Achievers ውስጥ ለተመዘገቡት ቅድሚያ የሚያሰጥ አይደለም።

**9.) እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች ለምን መጠቀም ይቻላል?**

የድጋፍ ገንዘቦች በቀጥታ ለሰራተኞች መከፈል አለባቸው። የሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታ አላማ ለልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ነው። ይህ ስጦታ ለልጅ እንክብካቤ ፕሮግራም የድጋፍ ገንዘቦች ለመስጠት የተነደፈ አይደለም። አቅራቢዎች የድጋፍ ገንዘቦችን አጠቃቀም በተመለከተ መዝገቦችን መያዝ እና ከተጠየቁ መዝገቦቹን ለከተማው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ይህ የድጋፍ ስጦታ ብቁ የሆኑ ተሸላሚ ሰራተኞች ወደ እነሱ የተላለፉትን የድጋፍ ገንዘቦችን በተመለከተ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ምንም ገደቦችን አያደርግም። እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች የሚቀበሉ ሰራተኞች የተሰጣቸውን የሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ ክፍያ እንዴት እንደሚያወጡ መዝግቦ መያዝ አይጠበቅባቸውም።

አቅራቢዎች የድጋፍ ገንዘቦችን ለመቀበል፣ በማመልከቻው ላይ፣ የድጋፍ ገንዘቦችን በFAQ መሰረት እና በማመልከቻው ውስጥ ባሉ ማናቸውም ተጨማሪ ድንጋጌዎች መሰረት ለመጠቀም መስማማት አለባቸው።

**10.) ከዚህ ከገንዘብ ድጋፍ ስጦታ ጋር በተዛመደ ደረሰኞችን እና መዝገቦችን ማስገባት ያስፈልገኛል?**

ፕሮግራሞች እነዚህ የድጋፍ ገንዘቦች ብቁ ለሆኑ ሰራተኞች የመከፋፈላቸውን ማስረጃ ማስቀመጥ አለባቸው። እነዚህ መዝገቦች/ ሪኮርዶች በሲያትል ከተማ ሊጠየቁ ይችሉ ይሆናል። በሲያትል ከተማ ልዩ ጥያቄ ካልቀረበ በስተቀር ለሰራተኞች የክፍያ ማስረጃ የማቅረብ ምንም መስፈርት/ ግዴታ የለም።

**11.) እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች ከመቀበል ጋር የተያያዙ ግብሮች እና ወጪዎችስ?**

የድጋፍ ገንዘብ ስጦታዎች እንደ ገቢ ይቆጠራሉ። ለግብር ዓላማዎች፣ የድጋፍ ገንዘብ ስጦታዎች (ይህን የማቆያ ክፍያን ጨምሮ) በንግድዎ ከተቀበሏቸው ሌሎች ገቢዎች ጋር በተመሳሳይ መልክ መወሰድ አለባቸው።

አቅራቢዎች እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች ለሠራተኞቻቸው ከማስተላለፍ ጋር የተያያዙ የንግድ ወጪዎችን ለመሸፈን ከተመደበው የድጋፍ ገንዘብ እስከ 15% የሚሆነውን ለማንኛውም ተዛማጅ ግብሮች እና/ወይም የአስተዳደር ክፍያዎች መያዝ ይችላሉ። የተረፈው ቀሪ ሂሳብ በፕሮግራምዎ በተለመደው የደመወዝ ክፍያ ስርዓት በኩል በቀጥታ ለሰራተኞችዎ መተላለፍ አለበት። ክፍያ በስጦታ ካርዶች መደረግ ወይም ቀጥታ የደመወዝ ክፍያ የማለፊያ-መንገድን በሌላ መተካት የለበትም። እባክዎን ማንኛውም የደመወዝ ተቀናሽ/ የክፍያ መያዣ ለእያንዳንዳቸው ሰራተኞች የመጨረሻውን የማካካሻ መጠን ይበልጥ እንደሚቀንስ ይወቁ።

ለምሳሌ፣ ተወካይ ድርጅትዎ በማመልከቻው ላይ 20 ሰዎችን ጠይቋል፣ እና እርስዎ $5,000 ዶላር ተቀብለዋል እንበል። ይህንን ወደ ሰራተኞችዎ የደመወዝ ክፍያ ቼኮች ለማስተላለፍ ማንኛውንም ግብሮችን ወይም አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመሸፈን ተወካይ ድርጅትዎ እስከ 15% (በዚህ ምሳሌ $750 ዶላር ይሆናል) እንዲይዝ ተፈቅዶለታል። ይህ ማለት በዚህ ምሳሌ ውስጥ ያለው ፕሮግራም ቢያንስ $4,250 ዶላር ለ20 ሰራተኞችዎ ለማስተላለፍ ይገደዳል፣ እያንዳንዳቸው የራሳቸው ቀረጦች እና የተያዙ ተቀናሾች ከመተግበራቸው በፊት እኩል መጠን ያገኛሉ።

እባክዎ የእርስዎን የተለየ የንግድ አንድምታ በተመለከተ ከባለሙያ የግብር አማካሪ ምክር ይጠይቁ።

**12.)የድጋፍ ስጦታዎቹ ሙሉ በሙሉ ይሰጣሉ?**

አዎ። ማመልከቻው ከጸደቀ/ ከተፈቀደ በኋላ፣ ሙሉ የድጋፍ ስጦታው መጠን እጅ በእጅ ይሰጣል። አቅራቢዎች በኤሌክትሮኒክ የባንክ ዝውውር (EBT) ወይም በቼክ ይከፈላቸዋል። ከዚህ ቀድሞ Child Care Resources ከነበረው ከ BrightSpark የቅድመ ትምህርት አገልግሎቶች የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ያልተሰጣቸው አቅራቢዎች፣ በዚህ ዘዴ ክፍያ የመፍቀድ አማራጭ ይሰጣቸዋል። ለአገልግሎት አቅራቢዎች ክፍያዎች ከነሐሴ ወደ መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥቅምት መጨረሻ ድረስ እንደሚሰጡ ይገመታል።

**13.)እነዚህን የድጋፍ ገንዘቦች ለሰራተኞቼ ማስተላለፍ ያለብኝ መቼ ነው?**

የአቅራቢው የድጋፍ ገንዘቦች መቀበልን ተከትሎ፣ የሰራተኛ ማቆያ ክፍያው በፕሮግራምዎ መደበኛ የደመወዝ ክፍያ ስርዓት በኩል በሚቀጥሉት ሁለት መደበኛ የክፍያ ወቅቶች ውስጥ መጠናቀቅ አለበት።

**14.)በሲያትል ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸው ብዙ የልጅ እንክብካቤ ጣቢያዎች ያሉኝ ተወካይ ድርጅት ከሆንኩ፣ ለእያንዳንዱ ጣቢያ የተለያየ ማመልከቻዎች ማቅረብ አለብኝ?**

አዎ። ፕሮግራሞች እንደ የማመልከቻው አንድ አካል የንግድ ስማቸውን እና በ DCYF የተሰጠ የአቅራቢ መታወቂያ# ይጠቅሳሉ። እያንዳንዱ ማመልከቻ ልዩ የሆነ በ DCYF የተሰጠ የአቅራቢ መታወቂያ# ሊኖረው ይገባል።

**15.)እኔ ምን ሰነድ ማቅረብ ይኖርብኛል?**

ከሽልማት ማሳወቂያ በኋላ፣ የተጠናቀቀ እና የተፈረመ W-9 እና የፕሮግራምዎን የDCYF የልጅ እንክብካቤ ፍቃድ ቅጂ ማስገባት ያስፈልግዎታል። እነዚህ ሰነዶች ቀድሞውኑ መዝገብ ላይ ካሉ ወይም ለዚህ የድጋፍ ስጦታ በተለየ መላክ ካለባቸው BrightSpark ለአመልካቾች ያሳውቃል።

ተፈጻሚነቱ የፀና ስምምነት በድጋፍ ስጦታ ማመልከቻ ውስጥ ይካተታል። አመልካቾች በማመልከቻው ቅጽ ላይ "አዎን፣ እስማማለሁ" የሚለውን ወይም የሚታየውን ማንኛውም አዎንታዊ ቋንቋ መምረጥ አለባቸው።

**16.)የሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ ክፍያ ወደ ባንኬ በኤሌክትሮኒክ መንገድ እንዲላክ ከፈለግኩ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ይህ የግዴታ መስፈርት አይደለም፣ ወይም ክፍያ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ለመቀበል ለሚመርጡ ፕሮግራሞችም የተሰጠ ምንም ዓይነት ምርጫ የለም።

ክፍያ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ መቀበል የሚፈልጉ እና ከBrightSpark ጋር በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስምምነት እንዲሁም ሰነድ የሌላቸው ፕሮግራሞች ለቀጥታ የተቀማጭ ሂሳብ ማስገቢያ ቅጽ የተጠናቀቀ ፍቃድ እና ባዶ ቼክ ወይም ከባንክዎ የሂሳብዎን እና የማዛወሪያ/ የማስተላለፊያ ቁጥር የያዘ ደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ክፍያ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዲተላለፍ፣ እነዚህ ሰነዶች ነሐሴ 23 ቀን 2023 ከማለቁ በፊት ሙሉ በሙሉ መድረስ አለባቸው። ለቀጥታ ተቀማጭ ገንዘብ ማስገቢያ የተሟላ የሥልጣን ፈቃድ እንዲሁም በ BrightSpark መዝገብ ላይ የባንክ ሰነዶች ለሌላቸው ተሸላሚዎች የወረቀት ቼኮች ይላካሉ።

### 17.)እንዴት ነው የማመለክተው?

ማመልከቻው በሰኔ ወር 2023 አጋማሽ ላይ እንዲገኝ መርሐግብር ተይዞለታል። የማመልከቻው አገናኝ በሲያትል ከተማ ይለጠፋል እንዲሁም በ BrightSpark በተላከ ኢሜይል በኩል ይታተማል። እንዲሁም አቅራቢዎች ማመልከቻውን በpdf ቅርጸት ሊጠይቁ ይችላሉ እና ወደዚህ ኢሜይል አድራሻ መላክ ይችላሉ: DEELfunding@seattle.gov። ማመልከቻው በሚከተሉት ቋንቋዎች ይገኛል: በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በተቃለለ ቻይንኛ፣ በኦሮምኛ፣ በሶማሊኛ፣ በስፓኒሽ እና በቬትናምኛ።

### 18.)ለዚህ የድጋፍ ስጦታ ለማመልከት የማብቂያ ጊዜ ገደብ አለው?

አዎ። ለማመልከት የማብቂያ ጊዜ ገደቡ ማክሰኞ፣ ሐምሌ 5 ቀን 2023 እስከ ሌሊቱ 11:59 ሰዓት በፓሲፊክ የቀን ብርሃን ጊዜ አቆጣጠር ነው።

### 19.)ማመልከቻውን ለመሙላት እርዳታ ቢያስፈልገኝስ ምን ላድርግ?

በ Early Achievers ውስጥ ተመዝግበው ከሆነ፣ ለእርዳታ የእርስዎን አሰልጣኝ መገናኘት ይችላሉ። በ Early Achievers ውስጥ ተመዝግበው ካልሆነ ወይም አሰልጣኝዎ ማን እንደሆነ ካላወቁ፣ እባክዎን የBrightSpark አቅራቢ መስመርን በ1-800-446-1114 ያግኙ፣ አማራጭ 2ን ይምረጡ። እንዲሁም ጥያቄዎች ወደ BrightSpark ሰራተኞች በ grants@childcare.org ሊላኩ ይችላሉ።

### 20.)ከሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች እንዳይለቁ የማቆያ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ከተሰጠኝ እንዴት እና መቼ ማሳወቂያ ይደርሰኛል?

ሁሉም ማመልከቻ ያስገቡ አቅራቢዎች የድጋፍ ስጦታ ሽልማት ሁኔታቸውን በኢሜይል በኩል ይነገራቸዋል። የሽልማት ማሳወቂያዎች በነሐሴ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ ይላካሉ። የክፍያው መጠን እና ብቁ የሆኑ ሰራተኞች ቁጥር በሽልማት ማሳወቂያው ላይ ይዘረዘራሉ።

ለአገልግሎት አቅራቢዎች ክፍያዎች ከረፋዱ ነሐሴ እስከ ጥቅምት መጨረሻ ድረስ እንደሚሰጡ ይገመታል።

### 21.)ማመልከቻው ከገባ በኋላ አንድ ሰራተኛ ፕሮግራሜን ቢለቅስ?

በልጅ እንክብካቤ ጣቢያዎ በማመልከቻው ላይ ብቁ ተብለው ከተቆጠሩት ሰራተኞች ውስጥ ከዚያ ወዲህ ተቀጥረው የማይሰሩ ካሉ እና ይህ እርስዎ ብቁ እንደሆኑ ከገለፁት የሰራተኞች ብዛት 25% ወይም ከሱ ያነሰ የሚወክል ከሆነ፣ ፕሮግራሙ ሙሉውን የሲያትል የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች የማቆያ ክፍያ ሽልማት በአሁኑ ጊዜ ተቀጥረው ለሚገኙ ብቁ ሰራተኞች በእኩል መጠን ማከፋፈል አለበት። እባክዎን ያስተውሉ፣ ብቁ ለመሆን፣ ቢያንስ ከኅዳር 1 ቀን 2023 ጀምሮ በልጅ እንክብካቤ ጣቢያው ተቀጥሮ መቆየቱን ጨምሮ፣ አንድ አባል ሰራተኛ ከላይ በጥያቄ #2 ያሉትን ሁሉንም የብቃት መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

በማመልከቻው ላይ ብቁ እንደሆኑ ሪፖርት ካደረጓቸው ሰራተኞች ከ 25% በላይ የሚሆኑት በእርስዎ ፕሮግራም ውስጥ ከዚያ ወዲህ እየሰሩ ካልሆነ፣ የሽልማት መጠንዎ እንደገና መሰላት የሚያስፈልገው ሲሆን DEELfunding@seattle.govን ማግኘት አለብዎት።